# የገጠር መሬት ሥሪት በኢትዮጵያ :- በሕግ የተደነገጉ መብቶችና በአማራ ብሔራዊ ክልል ያለው አተገባበር

ሞላ መንግሥቱ*

## መግቢያ

የሕግ መብት አንድ ሰው በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ደረጃ መገለጫ ነው። መብት ደግሞ የተለያዩ ገጽታዎች ያሉት ፅንሰ ሃሳብ ነው። ከእነዚህ ገጽታዎች የአንዱ አለመጠበቅ የአንድን ሰው ሰብእና የተሟላ እንዳይሆን ያደርገዋል። ከመብት ገጽታዎች አንዱ የንብረት መብት ሲሆን ይህ መብት የሰው ልጅ በሕግ ሊጠበቁለት የሚገባ መብቶች ሁሉ መሠረት ነው። የንብረት መብት በተለመደ ትርጉሙ የራስ በሆነ ነገር የመጠቀም ወይም የመገልገል በሕግ የተጠበቀ ሥልጣን ማለት እንደሆነ ተደርጐ ሲወሰድ እናያለን። የንብረት መብት የያዘው ትርጉም ግን ከዚህም የሰፋ ነው። ምክንያቱም የንብረት መብት የሚኖረው አንድ የራስ የሆነ ነገር ሲኖር ብቻ አይደለም። ይህም ማለት አንድ ሰው በባለቤትነት የያዘው አንድ ግዙፍ ነገር ባይኖረውም የንብረት መብት ግን ይኖረዋል ማለት ነው። ለምን ቢባል አንድ ግዙፍ ነገር መደፊት የማግኘት መብትም የንብረት መብት ስለሆነ ነው። ከዚህም ሌላ የንብረት መብትና በባለቤትነት የሚያዘው ነገር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ነገሮች አይደሉም። ምክንያቱም የንብረት መብት በሕግ ትርጉም የሚኖረው አንድ መብት አለኝ የሚል ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ሲታይ እንጅ መብቱ ከሚተገበርበት ነገር ጋር ካለው ግንኙት አንፃር ሲታይ ባለመሆኑ ነው።

ስለዚህም የንብረት መብት ማለት አንድ ሰው ምን ምን ነገሮችን በባለቤትነት ወይም ከባለቤትነት ባነሰ ደረጃ የያዘውን ነገር ለመገልገልና ለመጠቀም የሚችልበት ሁኔታ ያለውን ስፋትና ገደብ የሚያስረዳና የያዘውን ነገር ሲገለገል ያለውን ነፃነት በማክበር ሌሎች ሰዎች ጣልቃ ላለመግባት ያለባቸውን ገደብ የሚያስረዳ ሥልጣን ማለት ነው። ከዚህ ትርጉም የምንረዳው ደግሞ የንብረት መብት እንዲኖር በሰዎች መካከል ማህበራዊ ግንኙነት መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን ነው።ይህም የሚያስገነዝበን አንድ ሰው ያለው የንብረት መብት እንዲኖር በሰዎች መካከል ማህበራዊ ግንኙነት መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ያለው የንብረት መብት ሌሎች ሰዎች ይህን መብት ለማክበር ካለባቸው ግዴታ ጋር በእጅጉ የተሣሰረና ከዚህ አንጻር ካልታየም የንብረት መብት የሰውና የእቃ ግንኙት እንደሆነ ተደርጎ እንዲታይ ስለሚያደርገው ነው።

የንብረት መብት አንዱና በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላቀር አገሮች ዋናው መሠረት ደግሞ መሬት ነው። ምክንያቱም ለአብዛኛው ዜጋ ሌላ የሥራ መስክ፣ ሌላ የገቢ ምንጭ፣ ሌላ በሀብትነት የሚያዝ ነገር በሌለበት ሁኔታ እንኳን የንብረት መብት ህልውና እና

* Currently a Lecturer, formerly Associate Dean of the Faculty of Law, Addis Ababa University; he took part in the drafting of the current Amhara National Regional State Rural Land Use and Administration Proclamation; he holds LL.M; MA and LL.B. E-mail: mollamen@law.aau.edu.et

ማንነትም ከመሬት ጋር የተሣሰረ በመሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ አብዛኛው በገጠር ነዋሪና ኋላ ቀር በሆነ የግብርና ሥራ የሚተዳደር በመሆኑም በተለይ የገጠር መሬትን በተመለከተ ያለው የንብረት መብት የተመሠረተበት የመሬት ሥሪት ትክክለኛነትና የመብቱ በሰፋ ሁኔታ መከበር ለኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት መሠረት መሆኑ የማያከራክር ጉዳይ ነው።

የመሬት መብት መከበር የሚገለጸው በመሬት ሥሪቱ ትክክለኛ መሆን፣ ሥሪቱ ለተጠቃሚዎች በሚሰጠው መብት ስፋትና በመሬት አስተዳደሩ አመቺነት በአጠቃላይ ቢሆንም የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የገጠር መሬት ሥሪቱ ለአርሶ አደሮች የሚሰጠውን መብትና የመሬት አስተዳደሩን ከሕጉ አንፃር መተንተን እንጂ አሁን ያለው የገጠር መሬት ሥሪት ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጥያቄ መመለስ አይደለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ የመሬት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ ነው የሚለውን የሕገ መንግሥት ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች የገጠር መሬት መብት ከባለቤትነት የሚያንሰው መሸጥ ወይም በሌላ ንብረት መለዋወጥ ባለመቻል ብቻ ሆኖ ስለ መብቱ በበታች ሕጎች ጠቦ ተደንግጓል የሚለው አስተያየት የዚህ ጽሑፍ ዋና የክርክር ነጥብ ሲሆን የገጠር መሬት መብቱ በአማራ ብሔራዊ ክልል ያለውን አተገባበር መተንተንም ሌላው የጽሑፉ ትኩረት ነው። ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች አተገባበር ልዩነት የሚታይበት መሆኑን ለማመልከት ብቻ አግባብ በሆነበት ቦታ የሌሎች አንዳንድ ክልሎች የገጠር መሬት ሕጎችም ባጭሩ ይዳሰሳሉ። በታሰበው ሁኔታ ሃሳቦችን ለማቅረብ እንዲመችም ያለፈውን የኢትዮጵያ የገጠር መሬት ሥሪት በማስቀደም ጽሑፉ በተለያዩ ክፍሎች እንዲቀርብ ተደርጓል።

## 1. የቅድመ -1967 የገጠር መሬት ሥሪት አጭር ዳሰሳ[1].

የመሬት ሥሪት አርሶ አደሮችና ሌሎች የመሬት ተጠቃሚዎች መሬት የሚይዙበትን ሁኔታና የአጠቃቀሙን ሥርዓት የሚገልጽ ጽንሰ ሃሳብ ነው[2]። ይህ ትርጉም የመሬት ሥሪት መሬት ከማግኘት መብት የሰፋና የመብቱን ደረጃም ሆነ መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ተቋማትን የሚያካትት መሆኑን ያስገነዝበናል። ስለዚህም በአንድ አገር ያለው የመሬት ሥሪት ግንኙነት መሬት መጠቀምን በተመለከተ አንድ ሰው ከሌላው ሰው ጋር ያለው ማህበራዊ ግንኙነት የሚገለጽበት ጽንሰ ሃሳብ ነው ማለት ነው። ይህ የሚጠቁመን ደግሞ የመሬት ሥሪት በተለይ በግብርና በሚተዳደር ህብረተሰብ የግለሰቦችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ የሚገልጽ መሆኑን ነው።[3] በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች የህብረተሰቡን አባላት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ የሚገልጽ በመሆኑም የመሬት ሥሪት በአንድ አገር ለሚኖረው የዲሞክራሲ ግንባታም መሠረት ነው።

---

[1] ከ1967 ዓ.ም. በፊት በኢትዮጵያ የነበሩት የገጠር መሬት ሥሪት ዓይነቶች በአሁኑ ጊዜ ታሪክ ቢሆኑም
መጠናታቸው ግን ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

[2] Kenneth H. Parsons, Land Tenure, the University of Wisconsin press, Wisconsin (1963), P.44

[3] ibid P.4

4. Aberra Jembere, Legal History of Ethiopia 1434 – 1974: Some Aspects of Substantive and procedural Law, Leiden: Arika – Studiecentrum (1998) P. 123

ስለሚለያይ ነው እንጂ ሁለቱም ልክ ናቸው። ምክንያቱም የርስት ይዞታ መሬት የወል ባለይዞታ በሆኑት ርስተኞች መካከል መሬቱ ያለምንም ገደብ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ ይችላል።ይሁን እንጂ የርስት ይዞታ የርስተኞቹ የጋራ ይዞታ በመሆኑ ከርስተኞቹ ውጭ ለሆነ ሰው ግን ሊተላለፍ አይችልም።

የርስት ይዞታ መሠረቱ አንድን አካባቢ ማቅናትና መሬቱን በይዞታ ሥር ማድረግ ነው። እነዚህ የአንድ አካባቢ የመጀመሪያ አቅኚ የሆነ ሰው ተወላጆች ከጊዜ ወደ ጊዜ በአቅኚው አባታቸው የመሬቱ የጋራ ባለቤትነታቸው ተቀባይነት እያገኘ መጣ[9]። ስለዚህም የርስት ይዞታ ጥንታዊ መሠረቱ የቀዳሚነት ይዞታ መብት ነው ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ ነገሥታት ግዛታቸውን እያስፋፉና የማዕከላዊው አስተዳደር የተሻለ ጥንካሬ እያሳየ ሲመጣ በተለይ መሬት በቀላድ በተለካባቸው አካባቢዎች ከመሬቱ ሁለት እጁን ለራሱ አስቀርቶ አንድ እጁን ለባለይዞታዎች እንደተወላቸውና ለመንግሥት ከተያዘው ድርሻም ሲሦውን ለካህናት በመስጠቱ የቤተክርስቲያን ይዞታ በወል ሥሪቱ ውስጥ መመሥረቱን አንዳንድ ምንጮች ያስረዳሉ[10]።

የጥንት ባለይዞታዎችም ከመንግሥት ከተተወላቸው ሲሶ የመሬት ድርሻ ላይ ቤተክርስትያን እንዲተከል እያደረጉና ለካህናት መተዳደሪያቸውን እየሰጡ[11] የቤተክርስቲያን ሰበካንና የርስታቸውን ወሰን አንድ ማድረግ ቻሉ። በዚህም ምክንያት የአንድ የርስት ይዞታ መሬት ክልል መሬቱ በሚገኝበት ቤተክርስቲያን ሰበካ የተወሰነ እንዲሆን አደረገው። በአጠቃላይ ሲታይም የርስት ይዞታ በጋራ የተያዘና ለቤተሰብ በማንኛውም ሁኔታ ሊተላለፍ የሚችል ይዞታ ነው። የርስት ይዞታ በውስጡ ከቤተክርስቲያን ይዞታ ሌላ የጉልትና የርስተ ጉልት ይዞታም ይገኛል። የርስት ይዞታ የጋራ ይዞታ ቢሆንም ለሌላ ቤተሰብ ከማስተላለፍ በመለስ ለባለይዞታዎች የሚሰጠው መብት ሰፊ ነበር። የርስት ሥሪት ሰዎችን በአንድ አካባቢ የሚገኝ መሬት የጋራ ባለይዞታ የሚያደርገው የዘር ሃረግን ከአንድ የጋራ አባት ግንድ መሆን በመቁጠር በመሆኑ በአንድ በኩል በቁጥርጥር ዝምድናም እንኳ ቤተሰባዊ ግንኙነትን ስለሚያጠናክር ለህብረተሰቡ ሠላማዊ ኑሮ መሠረት የመሆን ከፍተኛ ማህበራዊ ጠቀሜታ ነበረው። በሌላ በኩል ግን ከተለያየ የቤተሰብ ግንድ በሚወለዱ ሰዎች መካከል ርስቱ የእኔ አባት ያቀናው እንጅ የእናንተ አባት ያቀናው አይደለም። ስለዚህም የርስተኝነት መብቱም የእኛ ነው በሚሉ የተለያዩ ቤተሰቦች መካከል ረጅም ዘመን የሚፈጁ ክርክሮች ምክንያት የነበረና አንዳንድ ጊዜም በዚህ ዓይነት ቤተሰቦች መካከል መጋደልን በማስከተል ከፍተኛ ጠላትነትን ሲፈጥር የነበረ ሥሪት ነው። ከዚህም በተጨማሪ አንደኛ የርስት ሥሪት ከቤተክርስቲያን ጋር በመተሳሰሩ የክርስትና እምነት የማይከተሉ የህብረተሰቡ ክፍሎችን የመሬት ባለይዞታ አያደርጋቸውም።

---

10 .ማህተመሥላሤ ወ/መስቀል ስለየኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደርና ግብር ጠቅላላ አስተያየት (ያልታተመ) ገጽ፡ 14

11.ማህተመ ሥላሴ ወ/መስቀል በቁጥር 10 እንደተጠቀሰው

ሁለተኛም የዘራቸውን ጥንታዊ አባት ቆጥረው ከአቅኚው ርስተኛ አባት ጋር በዝምድና ማገናኘት የማይችሉ ሰዎችም የመሬት ባለይዞታነት መብት አያገኙም። ይህ በመሆኑ ደግሞ የመሬት ይዞታ መብት ማግኘት የማይችሉት የህብረተሰቡ ክፍሎች ሁሉ የርስተኞች የመሬት ተጠማኝ ከመሆናቸውም ሌላ የሰዎች ማንነት የሚገለፀው ከርስተኝነት ጋር ተያይዞ ስለነበር በህብረተሰቡ ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃ እንዲታዩ አድርጓቸው ነበር።

የጉልት ይዞታ ለተፈፀመ ውለታ ለመንግሥት ባለመሬቶች የሚከፍሉትን ግብር ተቀብሎ ለግል ለመቀጠም እንዲቻል የሚሰጥ መብት ነው። ባለፈው ለተፈፀመና ወደፊትም ሊፈጸም የሚችል የአንድን አካባቢ የማስተዳደርና ፀጥታ የማስከበር ተግባር በግል የሚሰጥ "የመሬት ይዞታ" መብት በመሆኑ ለልጅ የሚተላለፍ ይዞታ አይደለም። መንግሥት ከፈለገም ጉልተኛው ተግባሩን አልተወጣም ብሎ ሲያምን መልሶ ሊወስደው ይችላል። ይህ ይዞታ ከርስት ይዞታ ጋር ትስስር ስለሌለው የርስት ሥሪት በሌለባቸው የአገሪቱ ክፍሎችም የነበረ ይዞታ ነው[12]።

የርስተ ጉልት ይዞታ ደግሞ በርስት ስሪት አካባቢዎች ከርስት ይዞታ በተጨማሪ በግል ይዞታ አካባቢ ደግሞ ከግል ባለቤትነት በተጨማሪ ከመሬቱ የሚሰበሰበውን ግብር ሰብስቦ ለግል ለመጠቀም ከመንግሥት የሚሰጥ መብት ሲሆን መብቱ የሚሰጠውም ለመንግሥት ለተሰጠ አገልግሎት ነው። በመሬቱ ላይ ካለ የርስተኝነት ይዞታ ወይም ከግል ባለቤትነት በተደራቢነት የሚሰጥ በመሆኑም መልሶ ሊወሰድ የማይችልና ለተወላጅ ሁሉ በማንኛውም ሁኔታ ሊተላለፍ የሚችል ይዞታ ነው[13]።

የግል የመሬት ሥሪት በአብዛኛው በደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል ተንሰራፍቶ የነበረ ሲሆን[14] ለእያንዳንዱ ባለይዞታ ሙሉ የመሬት ባለቤትነት መብት የሚሰጥ ሥሪት ነበር። በመንግሥት በግዴታ የተጣለ ሥሪት ስለነበርም ሥሪቱ ለሁሉም ዜጎች መሬት በግል ባለቤትነት የመያዝ መብት የሚሰጥ ቢመስልም የተወሰኑ ለመንግሥት ልዩ ቅርበት የነበራቸው ግለሰቦች ብቻ መሬቱን ሰብስበው ይዘው አብዛኛውን ህዝብ ግን መሬት አልባና የመሬት ተጠማኝ ያደረጉበት ሥርዓት ነበር። የመሬት የግል ባለቤትነት መብት ያለበት ሥሪት በመሆኑም መሬቱ በባለቤቱ ውሳኔ ሲሸጥ ወይም በሌላ ሁኔታ ለማንኛውም ሰው ሊተላለፍ የሚችልበት የይዞታ ዓይነት ነበር።

የመንግሥት ይዞታ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የነበረ ሥሪት ሲሆን መሬቱን መንግሥት ለሚፈልገው የራሱ ተግባር የሚያውልበት አለዚያም ለባለመዋለቹ እንደማደሪያ የሚሰጥበት ወይም ለመንግሥት ለሚገብር ተጠማኝ የሚሰጥበት የይዞታ ዓይነት ነበር[15]።

---

[12]. Aberra Jembere cited at note 4, P.141
[13] [13] ibid
14.id. P. 123

[15] ማህተመሥላሴ ወ/መስቀል በቁጥር 10 እንደጠቀሰው፣ Dessalegn Rahmato, Agrarian Reform in Ethiopia, Scandinavian institute of African Studies, Uppsala (1984), P.20

2. የድርው መጨረሻና የአዲሱ መጀመሪያ:- የ1967 ዓ.ም. የመሬት ሥሪት ለውጥ፣

በ1967 የተደረገው የመሬት ሥሪት ለውጥ በ1966 የተካሄደው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በአገሪቱ ያስከተለው አጠቃላይ የሥርዓት ለውጥ ውጤት አካል እንጅ ብቻውን የተከሰተ አልነበረም። ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን ተከትሎ የደርግ መንግሥት የዘውድ አገዛዙን ተክቶ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የአገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት ሶሻሊስታዊ ርዕዮተ ዓለምን እየተከተለ በመምጣቱ የኢኮኖሚ ሥርዓቱም አብሮ በመለወጡ የመሬት ሥሪት ለውጥ እንዲከተል አደረገ።

የገጠር መሬት ሥሪት ለውጡ በሕግ ሲታወጅም በመጀመሪያ አጽንኦት የሰጠው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በእርሻ የሚተዳደሩ አገሮች አንድ ሰው በህብረተሰቡ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው የኑሮ ደረጃ፣ መብት፣ እንዲሁም ክብርና ማዕረግ የሚወሰነው ከመሬት ጋር ባለው ግንኙነት በመሆኑ የዜጐችን እኩልነት ለማስከበር የመሬት ስሪቱን መለወጥ አስፈላጊ መሆኑን ነው[16]። ቀደም ብሎም እንደተመለከትነው ከ1967 ዓ.ም. ቀደም ብሎ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሰፍኖ የነበረው የመሬት ሥሪት ደግሞ ለሁሉም የአገሪቱ ዜጐች እኩል መብት የማይሰጥ በመሆኑ የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ መሬትን በተመለከተ ሊያከራክር የሚችለው ምን ዓይነት ለውጥ ይደረግ የሚለው ጉዳይ እንጅ የመሬት ሥሪቱ መለወጥ አስፈላጊነት አልነበረም።

አጠቃላይ የፖለቲካ ሥርዓቱ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ተከታይ በመሆኑም መሬትን የመሳሰሉ ሃብት ማፍሪያዎች የግል ባለቤትነት መብት በሥርዓቱ ተቀባይነት ስለማይኖረው የመሬት ሥሪቱ በአገሪቱ አንድ ወጥ ሆኖ "የሕዝብ ይዞታ" ተብሎ ታወጀ[17]። ስለዚህም ርስት ይዞታ፣ በግል ይዞታ ወይም በመንግሥት ይዞታ ሥር የነበረው የገጠር መሬት ሁሉ የህዝብ ይዞታ በመደረጉ ማንኛውም በእርሻ ለመተዳደር የሚፈልግ ሰው መሬት የማግኘት እኩል መብት እንዳለው ሕጉ ደነገገ። ይህ የመሬት ሥሪቱ መሠረታዊ መርህ ቢሆንም አንድ አርሶ አደር በመሬት ላይ ያለው የንብረት መብት ግን እንዲሁ ከላይ ስናየው ከሚመስለው እጅግ የጠበበ ነበር። የመጀመሪያው የመሬት መብቱ ውሱንነት የሚታየው የይዞታ መሬትን በሽያጭ፣ በለውጥ፣ በማውረስ[18] በማስያዝ፣ በወለድአገድ በመስጠት ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ በመከልከሉ ነው[19]። በዚህ ክልከላ ምክንያትም የመሬቱ ባለይዞታ ያለው መብት ከአንድ የመሬት ተከራይ ያላለፈና በግል እያረሱ የመጠቀም መብት ብቻ ነው።

---

[16] የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 31/1967 መግቢያ

17.በቁጥር 16 እንደተጠቀሰው አንቀጽ 3(1)

[18] ባለይዞታው ሲሞት/ስትሞት ግን የትዳር ጓደኛው ወይም አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ እነዚህ ከሌሉ ደግሞ አካለመጠን ያደረሰ ልጅ ተተክቶ በመሬቱ የመጠቀም መብት እንደሚኖረው በአንቀጽ 5 ተደንግጓል፡፡

19.ከላይ በቁጥር 16 እንደተጠቀሰው አንቀጽ 5

የመሬት ሥሪቱ የህዝብ ይዞታ እንደሆነ በመታወጁ መሬት ሊሸጥ የማይችል ሀብት መደረጉ ከራሱ ከሥሪቱ ባህሪ የሚመነጭ መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም ማከራየትንም ጨምሮ በሌላ ሁኔታ የመሬት ይዞታ መብትን መገልገልንም መከልከሉ ግን ሥሪቱ ለባለይዞታዎች የሰጠውን መብት ጠባብነት የሚያመለክት ነው። አዋጁ ከዚህም አልፎ በእርጅና ወይም በህመም ወይም አካለመጠን ባለማድረስ ወይም ለሴቶች ካልሆነ በስተቀር በይዞታ መሬት ላይ ሌላ ሰው ቀጥሮ ማሳረስም መከልከሉን ስንመለከት በሕግ የተሰጠውን መሬት የማግኘት እኩል መብት በተግባር ለመጠቀም ያለውን የመብት ጠባብነትና አስቸጋሪነት እንረዳለን።

በ1980 የወጣው የኢሕድሪ ሕገ መንግሥትም የገጠር መሬት ሥሪትን በተመለከተ ቀደም ብሎ ከታወጀው ሥሪት የተለየ ምንም ያስከተለው ለውጥ አልነበረም።ስለዚህም አዲሱ የገጠር መሬት ሥሪት በአንድ በኩል የተወሳሰበና ለተወሰኑ ዜጐች መብት በመስጠት ለአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ግን መብት የሚነፍገውን ነባሩን የመሬት ሥሪት በማስወገዱ መልካም ገጽታ ያለው ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ለባለይዞታዎች ከግል ባለቤትነት መብት በመለስ እንኳ መጠበቅ የሚገባውን መብት እጅግ በማጥበቡና የመሬት አስተዳደሩንም በመንግሥት አካላትና የፖለቲካ ካድሬዎች ሥር በማድረጉ ከንብረት መብት አንጻር ይህ ነው የሚባል ለአርሶ አደሮች ከድሮው የመሬት ስሪት የተሻለ የመሬት የተጠቃሚነት ለውጥ ሳያስከትል ቀርቷል። ከዚህም በተጨማሪ የመሬት አስተዳደሩ ተቋም የህዝብ ተሳትፎው የይስሙላ የሆነበትና ለፖለቲካው ባለ ታማኝነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የመሬት ክፍፍሉን ፍትህ የጐደለው እንዲሆን ከማድረጉም በላይ በተለይ የርስት ይዞታ በነበረው የአገሪቱ ክፍል የመሬቱን ይዞታ የበለጠ እንዲበጣጠስ አደረገው። ይህም በመሆኑ በመጀመሪያው ለሥርዓቱ ለውጥ ምክንያት ከሆኑት መሠረታዊ ችግሮች አንዱ የነበረው የመሬት ሥሪት ችግር እንደገና የህብረተሰቡ አንድ የብሶት ምንጭ በመሆን በደርግ መንግሥትና በአርሶ አደሩ መካከል የነበረውን ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ እያሻከረው መጥቶ በርካታ አርሶ አደር የኢሕአዴግን ትግል በመደገፍ ለደርግ መውደቅ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ምክንያት ሆነ።

### 3. የ1983 የመንግሥት ለውጥና የገጠር መሬት ሥሪት ሁኔታ

የደርግን መንግሥት በ1983 ከሥልጣን ያስወገደው ኢሕአዴግ እንደ መታገያ ያነሳቸው ከነበሩ ጥያቄዎች አንዱ የደርግ መንግሥት የገጠር መሬት ጥያቄን በአግባቡ አልመለሰውም የሚለው ነበር። በዚህና በተለይም በአርሶ አደሩ በነበረው የመሬት አስተዳደር መከፋት ምክንያት ከመሬት ሥሪት እስከ መሠረታዊ የመሬት አስተዳደር ለውጥ ከአዲሱ መንግሥት የሚጠበቅ ተግባር ነበር። ይሁን እንጅ ቀደም ብሎ የነበረውን የሶሻሊስት ሥርዓቱ ውጤት የሆነውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ግንኙነት በተመለከተ ብዙም ሳይቆይ በአዲሱ መንግስት በግል ባለቤትነት ላይ ወደ ተመሠረተው የገበያ ሥርዓት ለውጥ የተደረገ ቢሆንም በገጠር መሬት ይዞታው ላይ ግን ዝምታው አጭር ለማይባል ጊዜ ሰፍኖ ቆየ። ሐምሌ 15/1983 የወጣው የሽግግሩ መንግሥት መመሪያ ቻርተርም አንዳንድ መሠረታዊ የፖለቲካ አቅጣጫዎችን ከመጠቆሙ[20] በስተቀር ስለመሬት ሥሪቱ ምንም ያመለከተው ነገር

---

[20] የሽግግሩ መንግሥት ቻርተር ቁጥር 1/1983 አንቀጽ 10

አልነበረም። ስለዚህም የሽግግሩ መንግሥት ቻርተር በአንቀጽ 11 በደነገገው መሠረት ቻርተሩ በሕገ መንግሥት እስኪተካ ድረስ የገጠር መሬት ሥሪቱ በነበረበት በመቀጠሉና የመሬት አስተዳደሩም የእለት ከእለት ችግሮችን በማቃለል ላይ ተወስኖ በመቆየቱ ስለመሬት የሥሪትም ሆነ የአስተዳደር ለውጥ ከሚወጣው አዲስ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ ሲጠበቅ ቆዩ።

### 3.1 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትና የገጠር መሬት መብት

የመሬት ይዞታ ጥያቄ በአጠቃላይና የገጠር መሬት ይዞታ በተለይ ቀደም ብሎ በተደጋጋሚ ሲነሳና ሲያከራክር እንደነበረው ሁሉ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ከመውጣቱ በፊትም በየስብሰባዎችም ሆነ በየግል ውይይቶች የመነጋገሪያ ነጥብ ሆኖ ነበር። የመሬት ሥሪቱ ምን መሆን አለበት በሚለው ነጥብ ላይም ያሳምናሉ የተባሉ ምክንያቶች እየተሰጡ የተለያዩ አቋሞችም ሲገለጹ የቆዩ ቢሆንም ሕገ መንግሥቱ ቀደም ብሎ በነበረው መንግሥት ከነበረው በተለየ ሁኔታ የአገሪቱ የንብረት ባለቤትነት መብት ሥርዓት በግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን በአጠቃላይ ደንግጎ የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በማስፋትና መብቱን ለማስጠበቅ መሠረት የሚሆኑ ድንጋጌዎች በማካተት የመሬት ሥሪቱን በተመለከተ ግን መሠረታዊ ለውጥ ሳያደርግ ወጣ[21]። ስለዚህም የሥሪቱን አይነትና የግል ባለቤትነት መብትን በተመለከተ ጥያቄው አሁንም ቀደም ብሎ ከነበረው ሥሪት መሠረታዊ ለውጥ በታየበት መልክ በዚህ ሕገ መንግሥት የተደነገገበትን ሁኔታ መረዳት አይቻልም።

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የተደነገገው የገጠር መሬትን "የመንግሥትና የሕዝብ" ያደረገው ሥሪት ለኢትዮጵያ ሁኔታ ከግል ባለቤትነት ይልቅ ምን ያህል ትክክለኛ ሥሪት ነው የሚለውን ጉዳይ መተንተን የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ባለመሆኑ ከዚህ በመቀጠል ሕጉ የገጠር መሬትን በተመለከተ ለባለ ይዞታዎች የሚሰጠው መብት ምንድን ነው የሚለውን ለማብራራት ይሞከራል።

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 የገጠር መሬትን በተመለከተ የሚደነግገው ሁለት መሠረታዊ ነጥቦችን ነው። እነዚህም አንደኛው የመሬቱ ባለቤትነት የመንግሥትና የህዝብ ነው የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መሬት ሊሸጥ ወይም ሊለወጥ አይችልም የሚለው ነው። ሁለቱም ነጥቦች ለገጠር መሬት ተጠቃሚዎች መብት የሚሰጡ ሳይሆኑ በተጠቃሚዎች መብት ላይ የተጣሉ ገደቦች ናቸው። በአጠቃላይም ሕገ መንግሥቱ የመረጠው በመሬት ላይ የተፈቀዱ መብቶችን በሙሉ ዘርዝሮ በመደንገግ ፋንታ አንድ የንብረት ባለመብት ሊኖሩት ከሚችሉ መብቶች መሬትን በተመለከተ የተከለከሉትን በዝርዝር ማስቀመጥን ነው። ይህም ማለት አንደኛ ማንም ሰው የገጠር መሬት የግል ባለቤት ሊሆን አይችልም ማለት ነው። ሁለተኛም ማንም ሰው የገጠር መሬትን በሽያጭ ወይም በገበያ ውስጥ አስገብቶ በሌላ ንብረት እንደ ሸቀጥ ሊለዋወጥበት አይችልም ማለት ነው።

---

[21] የሕገ መንግሥቱ 40(1) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት የመሆን መብት እንዳለው ሲደነግግ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ግን ከንዑስ አንቀጽ 1 በተለይ ሁኔታ የገጠርም የሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ መሆኑን ደንግጓል።

የመሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ነው ተብሎ መደንገጉ ራሱ መሬትን ከገበያ ሸቀጥነት ስለሚያወጣው የመሸጥም ሆነ በሌላ ንብረት የመለወጥ መብትን የሚያሳጣ በመሆኑ የተለየ አጽንኦት ለመስጠት ካልሆነ በስተቀር በድንጋጌው ውስጥ መኖሩ ካለመኖሩ የሚለየው ነገር ያለ አይመስለኝም።

ስለዚህም ይህን ድንጋጌ ብቻውን በማየት የምንገነዘበው በኢትዮጵያ የገጠር መሬት ሥሪት መሠረት አንድ የመሬት ተጠቃሚ አንድ የመሬት የግል ባለቤት ከሚኖረው መብት በተለየ የተከለከለው መሸጥና መለወጥን ብቻ ነው የሚለውን ነው። ይህ ማለት ደግሞ አንድ የግል የመሬት ባለቤት በመሬቱ ላይ ካለው በቀጥታ የመጠቀም ፣ ከመሬቱ የሚገኘውን ፍሬ በሌላ ሁኔታ የመሰብሰብና በሽያጭም ይሁን በሌላ መንገድ ንብረቱን የማስተላለፍ መብት ውስጥ ከመሸጥ ወይም በሌላ ንብረት ከመለዋወጥ በስተቀር ሌሎች መብቶች የገጠር መሬት ባለይዞታውም አሉት ማለት ነው። በተለይ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች እንዲሁም አርብቶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን የሚደነግጉትን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ስንመለከት ሕገ መንግሥቱ የመሬት ተጠቃሚዎችን ሲከለክል የፈለገው መሬትን እንደ ሸቀጥ በገበያ አስገብቶ ከአንድ ተጠቃሚ ወደሌላ ተጠቃሚ ማስተላለፍን ብቻ መሆኑን በበለጠ እንረዳለን።

የገጠር መሬት ሥሪቱ የመሬት ባለቤትነቱ የመንግሥትና የሕዝብ መሆኑና አርሶ አደሮች ከሚያገኙት መሬት ያለመነቀል መብት እንዳላቸው መደንገጉ የሚያስገነዝበው በመሬት ላይ የሚኖረው መብት የይዞታ መብት መሆኑን ነው። የመሬት የይዞታ መብት ደግሞ በይዞታ መብቱ ላይ ተመሥርቶ ከሚገኘው የመጠቀም መብት የተለየ ነው። ይህን ስንልም የባለቤትነት መብት፣ የይዞታ መብትና የመጠቀም መብት የተለያዩና ከመጀመሪያው ወደ መጨረሻው ቅደም ተከተል እየጠበቡ የሚመጡ መብቶች ናቸው ማለታችን ነው። ምክንያቱም የባለቤትነት መብት መሸጥን ጨምሮ ማንኛውንም በንብረት ላይ ሊኖር የሚችል መብት ሁሉ የሚያካትት ከመብቶች ሁሉ የሰፋ መብት ሲሆን የይዞታ መብት ደግሞ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መሠረት የገጠር መሬትን በተመለከተ አንድ የመሬት ባለቤት ሊኖረው ከሚችለው መብት ላይ በመሸጥ ወይም በመለዋወጥ መሬትን ለሌላ ማስተላለፍን ብቻ ለይቶ በመከልከል ሌሎችን መብቶች ግን የጠበቀ መብት ነው። የመጠቀም መብት ደግሞ አንድ የገጠር መሬት የይዞታ መብት ያለው ሰው ሌሎች መብቶችን ሳይጨምር በመሬቱ ለመጠቀም የሚኖረው መብት ነው። ስለዚህም የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው የይዞታ መብቱን እንደጠበቀ የመጠቀም መብቱን ብቻ ለይቶ ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል ማለት ነው። የዚህ ዓይነት የመጠቀም መብት ማስተላለፍ ደግሞ መብቱ ለተላለፈለት ሰው የሚሰጠው መብት በመሬቱ የመገልገል መብት ብቻ ነው። በዚህም ምክንያት የመጠቀም መብትን በኪራይ መስጠት ወይም የይዞታ መብትን በማያስተላልፍና የመጠቀም መብት ብቻ በሚሰጥ ሁኔታ በዋስትና ወይም በመያዣ መስጠት በሕጉ የተከለከለ አይደለም ማለት ነው።

የገጠር መሬት ሥሪቱን በተመለከተ ከላይ ከጠቀስነው አንቀጽ ድንጋጌዎች ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚገባው ሌላው ጥያቄ የይዞታ መብትን ከሽያጭ ወይም በሌላ ንብረት ከመለዋወጥ ውጭ በሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች በቁመና ወይም በሞት ጊዜ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ይቻላል

ወይ የሚለው ነው፡፡ በእኔ እምነት ሕገ መንግሥቱ በገጠር መሬት ላይ መከልከል የፈለገውን መብት ለይቶ በመሸጥም ሆነ በመለዋወጥ ማስተላለፍ አይቻልም ብሎ በግልጽ ማስቀመጡ የይዞታ መብትን በሌላ ሁኔታ ማስተላለፍን ፈጽሞ መከልከል አለመፈለጉን የሚያሳይ ነው፡፡ የመሬት ይዞታ መብት ሊተላለፍ የሚችለው ደግሞ በሽያጭና በልውውጥ ብቻ ሳይሆን በስጦታም ሆነ በውርስ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም የማስፈፀሚያ የበታች ሕጎች ይህን ጥያቄ እንዴት እንደመለሱት ወደፊት የምናየው ቢሆንም ከተመለከትናቸው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች አንፃር ግን መብቱ የተከለከለ እንዳልሆነ እንገነዘባለን፡፡ ሕገ መንግሥቱ ከላይ ለማብራራት የተሞከረውን የገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት የሰጠ ቢሆንም መሬትን የማስተዳደሩ ሥልጣን ግን ሙሉ በሙሉ ለመንግሥት በመስጠቱ[22] አርሶ አደሩ ያለውን መሬት የማግኘት መብት በተመለከተ ቢያንስ ከመርህ አንፃር በመንግሥት ፈቃደኝነት ላይ ጥገኛ ከመሆን አላወጣውም፡፡

የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት መሬትን በተመለከተ ስለሥሪቱ፣ ስለመብቱ ወሰንና ስለአስተዳደሩ በአጠቃላይ የደነገገውን ተፈፃሚ ለማድረግም በፌዴራል ደረጃ አሁን ለታሪክ ጠቀሜታው ብቻ የሚጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 89/1989 እና እሱን በመሻር ታውጆ አሁን በሥራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 456/1997 ወጥተዋል፡፡ አዋጅ ቁጥር 89/1989 የአርሶ አደሮችን የገጠር መሬት መብት በተመለከተ ብዙም ዝርዝር ድንጋጌ ያላካተተና ክልሎች እንዲያወጡ ለሚጠበቀው ዝርዝር ሕግም እንደ መመሪያ ሆኖ ለማገልገል ግልጽነት የሚጎድለው ሕግ ነበር፡፡ ሕጉ የገጠር መሬትን መጠቀምና ማከራየት እንደሚቻል አመልካች ድንጋጌዎች ቢይዝም[23] ውርስን በተመለከተ ግን የመውረስ መብቱን ከባለይዞታው ጋር አብሮ ነዋሪ ለሆነ ቤተሰብ ብቻ ወስኖ በመስጠቱ[24] ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ የባለ ይዞታው መብት መጥበብ የታየበት ሕግ ነበር፡፡ የዚህን ሕግ እነዚህና ሌሎች ችግሮች ለመፍታትም ይመስለኛል አዋጅ ቁጥር 456/1997 የወጣው፡፡ የገጠር መሬት መብቱ ያለውን አፈፃፀም ከዚህ በታች ለመተንተን የምንሞክረውም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ይሆናል፡፡

### 3.2 የገጠር መሬት መብት አተገባበር በአማራ ብሔራዊ ክልል

የገጠር መሬት መብት አተገባበርን በውል ለመረዳት በመጀመሪያ መመልከት ያለብን ለአተገባበሩ መሠረት የሚሆኑ ማዕቀፍና ዝርዝር ሕጎች መኖራቸውን ነው፡፡ ሁለተኛው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ደግሞ ያሉት ሕጎች የመሬት መብትን መጠን ምን ያህል በአግባቡ አስቀምጠውታል የሚለው ነው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ጉዳይ ደግሞ አርሶ አደሩ ያለው ፍትሕ የማግኘት መብትና የፍ/ቤቶች ተደራሽነት ናቸው፡፡

---

22 . የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 52(2) (መ) የክልል መንግሥታት የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትን እንደሚያስተዳድሩ ደንግጓል፡፡

23 አንቀጽ 2(3)

24. አንቀጽ 2(3) (5)

### 3.2.1. ለአተገባበሩ ያለው የሕግ መሠረት፣

የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 52(2) (መ) ክልሎች መሬትን የሚያስተዳድሩት የፌዴራሉን የመሬት ሕግ መሠረት አድርገው መሆን እንዳለበት በደነገገው መሠረት አዋጅ ቁጥር 456/1997 ለገጠር መሬት መብት አተገባበር ለክልሎች እንደ መመሪያ የሚያገለግል ሕግ ነው። የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ሕጎችም ይህንኑ አዋጅ መሠረት እንዲያደርጉ ይጠበቃል። አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንድ የመሬት ባለይዞታ ያሉትን መብቶች በበቂ ሁኔታ ባይዘረዝርም መጠቀም፣ ማከራየትና ማውረስ እንደሚችል ግን በጥቅሉ ይጠቁማል[25]።

የመሬት ይዞታ መብት ቀጥታ ውጤቱ መጠቀም በመሆኑ ሕጉም ባለይዞታው በተለያየ ሁኔታ መሬቱን ሊጠቀምበት እንደሚችል በበቂ ደንግጓል[26]። የማከራየት መብትን በተመለከተ ግን እንደሚቻል ይደነግግና የሚቻለው ግን "ባለይዞታውን በማያፈናቅል ሁኔታ ከሆነ ነው" የሚል አደናጋሪ ሐረግ በመጨመር ባለይዞታው መወሰን የሚገባውን ውሳኔ ወስኖ መብቱን ይገድበዋል። ማውረስን በተመለከተ ግን የቤተሰብ አባልን ጨምሮ በሕግ የመውረስ መብት ለተሰጠው ሰው ማውረስ እንደሚቻል በመደንገግ ለመውረስ መብት የሚኖራቸውን ሰዎች ግን ክልሎች በሕጋቸው እንዲወስኑ በሚጠቁም ሁኔታ በዝምታ ያልፈዋል።

በየክልሎች ሕጎች በዝርዝር ሲደነገጉ ሊጠቡም ሆነ ሊሰፉ የሚችሉትም እነዚሁ መብቶች ናቸው። በዚህ አዋጅ ከመሬት ባለይዞታዎች መብት ጋር በተያያዘ ያልተደነገገው የመጠቀም መብትን በዋስትና የማስያዝ መብት ነው። የሚደንቀው ግን የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለሀብት የመጠቀም መብቱን በዋስትና የማስያዝ መብት እንዳለው በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 8(4) የተደነገገ መሆኑ ነው። የኪራይ መብት ከይዞታ መብት ያነሰ በመሆኑ ሕጉ ይህን መብት ከተከራይ የተሻለ መብት ላላቸው የመሬት ባለይዞታ አርሶ አደሮች ሆን ብሎ ለመከልከል ፈልጎ ነው ያልደነገገው ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ መሬት ማግኘት የመሬት መብትን በዋስትና በማስያዝ በሚገኝ የገንዘብ ብድርና በቴክኒካዊ ድጋፍ ካልታገዘ ብቻውን የአርሶ አደሮችን ኑሮ ሊያሻሽል ስለማይችል የመብቱ መከበር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው[27]። ይሁን እንጂ መሬት የመጠቀም መብትን በመያዣ ወይም በዋስትና የማስያዝ መብት መከበር ግን ክልሎች የዚህን ሕግ ድንጋጌዎች ትርጉም በሚረዱበት ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

---

25 . አንቀጽ 2(4)፣ 5(1)(ለ)፣ 5(2)፣ 8(1)

26 .አንቀጽ 5(1)(ለ)፣ 10(1)

27.Kenneth H. Parsons, cited at note 2, P.66

### 3.3. የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕጐችና የገጠር መሬት መብት አተገባበር

#### 3.3.1. የመብቱ ይዘትና አተገባበር ያለፈው ገጽታ አጭር ዳሰሳ

ቀደም ብሎ በአብዛኛው በርስት ስሪት ይተዳደር የነበረው የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት እጅግ የተበጣጠሱ ማሳዎች የሚገኙበትና አካባቢውም እጅግ የተራቆተ አካባቢ በመሆኑ አግባብ የሆነ የገጠር የመሬት አስተዳደር መኖርን የግድ ይላል። የቆዳ ስፋቱ 17,700 ኪሎ ሜትር ስኩየር በሆነው በዚህ ክልል ነዋሪ የሆኑት 3.2 ሚሊዮን ገደማ የሚሆኑ አርሶ አደሮች በይዞታ ያላቸው የማሳ ብዛት 16 ሚሊዮን መሆኑን ስንገነዘብ[28] የመሬት ይዞታው ምን ያህል የተበጣጠሰና አንድ አርሶ አደር የሚኖረው አማካይ የማሳ ብዛትም መጠናቸው ከአውድማ ስፋት የማይበልጥ አምስት ቁርጥራጭ ማሳዎች እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህም በክልሉ የሚኖረው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ የአርሶ አደሮችን መሬት የማግኘት እኩል መብት፣ ከመሬት ይዞታ ያለመነቀል መብት፣ በይዞታ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት በተሟላ ሁኔታ የሚያስጠብቅ መሆኑ በፌዴራሉ ሕገ መንግስት በመሸጥ ወይም በመለዋወጥ ከማስተላለፍ በመለስ የተጠበቀውን መብት ለማስከበር ብቻ ሳይሆን መሬቱን የበለጠ ከመበጣጠስና ከመራቆት ለመከላከልም አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው።

ይሁን እንጂ የፌዴራሉን ሕገ መንግሥት ተከትሎ የመጀመሪያውን የፌዴራሉን የመሬት አስተዳደር ሕግ መውጣት ግን ቀድሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 16/1989 በዋናነት ትኩረት የሰጠው የመሬት ሽግሽግ እንደገና ማካሄድን ነው። በዚህም ምክንያት በክልሉ በተለይ ኢሕአዴግ በ1983ዓ.ም. በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ብቻ የመሬት ክፍፍሉ እንዲካሄድ ተደረገ[29]። የመሬት ክፍፍሉ እንዲካሄድ ያስፈለገውም የገጠሩ መሬት በአብዛኛው በቢሮክራቶችና በደርግ የገበሬ ማህበር ተመራጮች ተይዟል በሚል ምክንያት ስለ ነበር[30] የመሬት ክፍፍሉ በአብዛኛው ቢሮክራት፣ ቅሪት ፊውዳል ተብለው የተፈረጁ አርሶ አደሮችን ይዞታ አራት ጥማድ ብቻ በመተው

---

[28] ከአቶ ገበየሁ በላይ (የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ኤክስፐርት ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ)

29. አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ከ1983 ዓ.ም. በፊት ከደርግ አገዛዝ ነፃ የወጡ የክልሉ አካባቢዎች የመሬት ክፍፍሉ ቀደም ብሎ የተከናወነ በመሆኑ የአዋጁ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በ1983 ከደርግ አገዛዝ ነፃ በወጡት የክልሉ አካባቢዎች ነው በማለት ይደነግጋሉ።

[30]የአዋጁ መግቢያ .... የገጠር መሬት በጥቂት የሥርዓቱ አቀንቃኝ በነበሩ ቢሮክራትና የገበሬ ማህበር ተመራጮች በመያዙ ምክንያት ሰፊ የይዞታ አለመመጣጠን ስለሚታዩ የመሬት ሽግሽግ ማካሄድ እንዳስፈለገ ይደነግጋል።

31.ሞላ መንግሥቱ፣ የንብረት መብት በኢፌዲሪ ሕገመንግሥት 1992 (ያልታተመ) ገጽ 22 የአዋጁ ማስፈፀሚያ ተደርጐ ሲሠራበት የነበረው የሽግሽግ መመሪያ ቢሮክራትና ቅሪት ፊውዳሎች ተብለው ለተፈረጁ ገበሬዎች የሚሰጣቸውን ከፍተኛ የመሬት መጠን ከሌሎች ገበሬዎች የሚሰጣቸውን ከፍተኛ የመሬት መጠን ከሌሎች ገበሬዎች ለይቶ በአንድ ሄክታር በመወሰኑ ክፍፍሉ ሌላ ኢፍትሐዊነትን አስከትሏል በማለት ተከራክሯል።

ሌላውን እየቀነሱ በማከፋፈል ላይ ያተኮረ ስለነበር ከፍተኛ የፍትህ ጉድለትና ፖለቲካዊ ገጽታ የታየበት የመሬት ክፍፍል ሆኖ አለፈ[31]።

አዋጁ ከዚህ ውጪ የባለይዞታዎችን መብት ማስከበርን በተመለከተ የደነገገው የመሬት ድልድሉ ከተጠናቀቀ በኋላ የገጠር ባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጥ መሆኑን ብቻ ነበር። በዚህም ምክንያት አዋጁ የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በዝርዝር በመደንገግም ሆነ በማስጠበቅ ያልተሟላ ከመሆኑም በላይ በሕጉ የተደነገገው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትም በወጉ ተግባራዊ ሳይሆን ያለፈውን ኢፍትሐዊ የመሬት ይዞታ አስተካክላለሁ በሚል ሌላ የሽግሽግ ኢፍትሐዊነት ተፈጽሞበት በአዋጅ ቁጥር 46/1992 የተተካ አዋጅ ነበር።

አዋጅ ቁጥር 46/1992 የገጠር መሬት የማግኘት መብትን፣ በይዞታ የመጠቀም መብትን፣ ለይዞታ መብት መጠበቅ ዋስትና መስጠትን በተመለከተ በመደንገግ የይዞታ መብት ያካተታቸውን መብቶች በአጠቃላይ በመደንገጉ ካለፈው ሕግ የተሻለ ሆኖ ቢታይም ከፍተኛ ውሱንነቶች የነበሩት ሕግ ነበር። ምክንያቱም አንደኛ መሬት የማግኘት መብት ተግባራዊ የሚሆንበት አንዱ መንገድ የመውረስ መብት ሲሆን ይህን መብት ግን ከባለይዞታው ጋር አብረው ለሚኖሩ ለቤተሰብ አባላትና የመሬት ባለይዞታውን መሬቱን እያረሰ ለጦረው ሰው ብቻ ሰጥቷል። ሁለተኛም በይዞታ የመጠቀም መብት ተግባራዊ የሚሆንበት አንዱ መንገድ የማከራየት መብት በሕጉ ቢደነገግም የኪራይ ዘመኑንና ሌሎች ዝርዝር ስርዓቶችን የሚደነግግ ደንብ ባለመውጣቱ መብቱን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም። ከዚህም በተጨማሪ ሕጉ የመጠቀም መብትን በዋስትና ስለማስያዝ ምንም ነገር ባለመደንገጉ የሰጠው መብት ውሱን እንዲሆን አድርጎታል። በሦስተኛ ደረጃም ሕጉ የይዞታ ዋስትና መጠበቅን በአንቀጽ 6(3) እና አንቀጽ 8 የደነገገ ቢሆንም የመሬት ሽግሽግ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ሊካሄድ እንደሚችል በአንቀጽ 10 በመደንገጉ በሕጉ ተጠብቋል የተባለውን የመሬት ይዞታ ዋስትና መልሶ ስጋት ላይ ጥሎታል። ይህ ደግሞ ለመሬት ተገቢው እንክብካቤና ጥበቃ እንዳይደረግ ምክንያት በመሆኑ የመሬቱን የበለጠ መጎሳቆል ከማስከተሉም በላይ በመሬት ላይ አስፈላጊውን ወጭ አውጥቶ በማልማት የምርት እድገት እንዲመጣ ለማድረግ ጉጉት እንዳይኖር አድርጓል። በመጨረሻም የመሬት መብት መሠረቱ ፍትህ የማግኘት መብት ሆኖ ሳለ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 16/1989 አንቀጽ 22(1)(ሀ-ሐ) የተሰጠው መሬትን የሚመለከት አቤቱታ ለፍ/ቤት የማቅረብ መብት በአዋጅ ቁጥር 20/1989 በአንቀጽ 14(2) ለማህበራዊ ፍ/ቤት በስልጣንነት በመስጠቱና የይግባኝ መብቱም በወረዳ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭነት በአንቀጽ 30(1) በመወሰኑ የባለይዞታው በመደበኛ ፍ/ቤት ፍትህ የማግኘት መብት እጅግ የጠበበ እንዲሆን አድርጎት ነበር።

### 3.3.2. የመብቱ ይዘትና አተገባበር አሁን ያለበት ሁኔታ

የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፖሊሲ የመሬት ይዞታ መብት መሠረታዊ መገለጫ ከሆኑት መካከል ይዞታን በውርስ የማስተላለፍና የመጠቀም መብትን በሙሉ ወይም በከፊል የማከራየት መብትን ማስከበር ዓላማው መሆኑን

ይደነግጋል። ከይዞታ ያለመነቀል ዋስትናን ለማረጋገጥም በሕዝቡ በራሱ ጥያቄ ካልቀረበ በስተቀር በክልሉ የመሬት ሽግሽግ እንደማይካሄድም ያስረዳል[32]። የዚህ ፖሊሲና የፌዴራሉ አዋጅ ቁጥር 456/1997 ተግባራዊ ማድረጊያ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 ደግሞ የክልሉ የመሬት ባለይዞታዎች የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት በግልጽ ካስቀመጣቸው ገደቦች በመለስ ሌሎችን አብዛኛዎችን መብቶች ለማካተት ሞክሯል።

ከላይም ለመጥቀስ እንደሞከርነው የገጠር መሬትን በተመለከተ በሕገ መንግሥት በግልጽ የተከለከለው መሸጥና መለወጥ ነው። መሸጥ ወይም መለወጥ ደግሞ የንብረት መብት ከሚገለጽበትና ተግባራዊ ከሚደረግባቸው መንገዶች አንዱ እንጅ ብቸኛው አይደለም። ስለዚህ መብት መከልከል መሠረቱ የመሬት ባለቤትነት መብት ለመሬት ባለይዞታዎች አለመስጠት ቢሆንም በንብረት መብት ላይ የመሸጥ መብትን መገደብ ደግሞ ከኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እንደምንረዳው በግለሰቦች መካከል ከሚደረግ ውልም ሊመነጭ ይችላል[33]። ስለዚህ መሬትን ያለመሸጥ ወይም ያለመለወጥ ሕገ መንግሥታዊ ገደቡ ወይም ከውል የሚመነጨው ንብረትን ያለማስተላለፍ ግዴታ ሌሎችን የንብረት መብቶች ተግባራዊ ከማድረግ ወሰን የሚያበጅ ሆኖ መታየት አይኖርበትም።

### 3.3.2.1. በውርስ ወይም በስጦታ የማስተላለፍ መብት

ከመሬት ጋር በተያያዘ ባለይዞታው ከመሸጥና ከመለወጥ ውጭ የሚኖሩት መሠረታዊ መብቶች ማውረስ፣ በስጦታ መስጠት፣ የመጠቀም መብቱን ማከራየት፣ የመጠቀም መብቱን በይዞታ ማስያዝ፣ ከይዞታ ከመነቀል የመጠበቅ መብትን የሚያካትቱ ናቸው።

የማውረስ መብት መከበር አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን ለመንከባከብ፣ አስፈላጊ የሆነውን የጉልበትና የገንዘብ ወጭ አውጥቶ መሬቱን ለማልማትና አካባቢን በአግባቡ ለመጠበቅ ምክንያትና ፍላጎት እንዲኖረው ለማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የባለይዞታው ተወላጆች ከባለይዞታው ጋር ባሉበት ጊዜም ሆነ ራሳቸውን ከቻሉ በኋላ ወደፊት መሬቱ ለእኔ ይተርፋል በሚል እምነት መሬቱ የሚያስፈልገውን እንክብካቤና ጥበቃ ለማድረግ የሚያስፈልገውን እገዛ እንዲያበረክቱ ሊገፋፋቸው ይችላል። ከዚህ በበለጠ ግን በአማራ ብሔራዊ ክልል በሥጋ ዝምድና ላይ የተመሠረተው የርስት ሥሪት ገንብቶት የነበረውንና የርስት ይዞታ ሲፈርስ አብሮ የመፈራረስ አዝማሚያ ያሳየውን ቤተሰባዊ በዝምድና ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መልሶ ለመጠገን ትልቅ መሠረት ይሆናል።

ለአዲሱ ትውልድ ሊሰጥ የሚችል ትርፍ መሬት በሌለበት የክልሉ ሁኔታ፣ ውርስ መሬት ከወላጆች ወይም ሌሎች ቤተሰቦች ለተወላጆች የሚሰጥበት ዋናው መንገድ በመሆኑም

---

32 . አንቀጽ 4.1.2.2 - 4.1.3.2.

33 የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ1428(1) “ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሀብትነትን ለሌላ ሰው የሚያስተላልፍ ሰው ንብረቱ የተላለፈለትን ሰው ንብረቱን እንዳይሸጥ፣ እንዳያስተላልፍ ለመከልከል ወይም ንብረቱን ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ያለውን ሥልጣን ለመቀነስ ይችላል በማለት ይደነግጋል።

የገጠር መሬትን ማውረስ እንደማንኛውም ንብረት በአውራሹ ፈቃድ ላይ ተመስርቶ በሕግ ሊጠበቅ የሚገባው መብት ነው፡፡ ይሁን እንጅ ይህን መብት ማስከበርን በተመለከተ በፌዴራሉ ሕገመንግሥት የተደረገ ገደብ ባይኖርም የተለያዩ ክልሎች የገጠር መሬት ሕጐች ያካተቱዋቸው ድንጋጌዎች ግን ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ ለምሳሌም የትግራይ ብሔራዊ ክልል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ አንድ አርሶ አደር መሬቱን በውርስ መሬት ለሌለው ልጁ ወይም የልጅ ልጁ ወይም ወላጁ መስጠት እንደሚችል በመደንገግ የማውረስ መብትን በእነዚህ ወራሾች ብቻ ወስኖታል፡፡

ይኸው አዋጅ ስጦታን በተመለከተ ግን አንድ አርሶ አደር ከቤተሰቡ በስጦታ የገጠር መሬት ማግኘት እንደሚችል ከመደንገግ በስተቀር ዝርዝሩን አላስቀመጠም፡፡ ቤተሰብ የሚለው ቃልም በአዋጁ ትርጉም ያልተሰጠው በመሆኑ[34] በፌዴራሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል ከተባለ በስጦታ የመስጠት መብት እጅግ የጠበበ ይሆናል፡፡ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ በበኩሉ የመሬት ይዞታ መብትን ማውረስ የሚቻለው ለቤተሰብ አባላት ብቻ እንደሆነ ሲደነግግ የቤተሰብ አባል ማለትም የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ ገቢ በመጋራት ከባለይዞታው ጋር በቋሚነት አብሮ የሚኖር ሰው[35] ማለት እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ለመሬት ባለ ይዞታዎች በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የተሰጠውን የይዞታ መብትን የማስተላለፍ መብት አጥብቦ የሚያስቀምጥ ድንጋጌ ነው፡፡ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ደግሞ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ በውርስ ሕግ መሠረት የመውረስ መብት ላለው የቤተሰቡ አባል የማውረስ መብት እንዳለው ገልጾ የቤተሰብ አባል የሚለውን ሐረግም ከባለ ይዞታው የተወለዱ ልጆች ወይም ሌሎች መተዳደሪያ ገቢ የሌላቸውና በቋሚነት ከባለይዞታው ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው[36] በማለት ይተረጉመዋል፡፡ በዚህ ሕግ መሠረትም የማውረስ መብት ለልጆችና በቋሚነት አብረው ለሚኖሩ ያውም ሌላ መተዳደሪያ ለሌላቸው ሰዎች ብቻ ተወስኖ ይታያል፡፡ ለዚህ የገጠር መሬት ይዞታ መብትን የማውረስ መብት መወሰንና ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል መለያየት መሠረት የሚሆን የበላይ ሕግ ግን አናገኝም፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ደግሞ የገጠር መሬት ይዞታን በስጦታ ወይም በውርስ ማስተላለፍ እንደ ሚቻል በግልጽ ደንግጓል[37]፡፡ የይዞታ መብትን በስጦታ መስጠት የሚቻለው ግን ለማንኛውም ሰው ሳይሆን በግብርና ሥራ ለሚተዳደር በቂ መሬት ለሌለው ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ወይም የቤተሰብ አባልና ባለይዞታውን መሬቱን እያረሰ ወይም ሌላ ሥራ እየሠራ ከሥጦታው በፊት ቢያንስ ለሦስት ተከታታይ አመታት ለጦረ ማንኛውም ሰው ነው፡፡ ይህ አዋጅም ስጦታ ሊሰጣቸው የሚችል ሰዎችን በመዘርዝር ስጦታ የመስጠት መብትን ውሱን አድርጐታል[38]፡፡ ባለይዞታው መሬቱን ማውረስ የሚችለውም በኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ እንደሆነም በሕጉ ተደንግጓል፡፡

[34] የትግራይ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 136/2000 አንቀጽ 5(2)፣ 17(1)(2)
[35] አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 2(7) እና 8(5)
[36] አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 2(17) እና 9(1)
[37] አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 15(1)
[38] በቁጥር 37 የተጠቀሰው አንቀጽ 17(1)

የይዞታ መብት በኑዛዜ ማስተላለፍ የሚቻለው በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ማንኛውም ሰው ቢሆንም ኑዛዜው ለአካለመጠን ያልደረሰ የሚች ልጅን ወይም ቤተሰብን ከወራሽነት የሚነቅል ሆኖ ከተገኘ ብቻ ግን ኑዛዜው ተቀባይነት እንደማይኖረው ገደብ ሆኖ እናገኘዋለን[39]::

የገጠር መሬት ባለ ይዞታው የመሬት መብቱን በተመለከተ ሳይናዘዝ ከሞተ ደግሞ ለአካለ መጠን ያልደረሱ የሚች ልጆች፣ አካለመጠን ያልደረሱ ሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ አካለመጠን ያደረሱ ምንም መሬት የሌላቸው የሟች ልጆች፣ አካለመጠን ያደረሱ ምንም መሬት የሌላቸው ሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ መሬት ያላቸው የሟች ልጆች፣ የሟች ወላጆች በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት ማውረስ እንደ ሚቻል በአዋጁም ሆነ በደንቡ ተደንግጓል[40]::

የአማራ ብሔራዊ ክልል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ የይዞታ መብትን በስጦታ ወይም በውርስ ማስተላለፍን በተመለከተ በፌዴራሉ ሕጎች የተቀመጠ ገደብ እንደሌለ ከተመለከትነው አንፃር አንዳንድ ገደቦች ቢታዩበትም ከሌሎች ከላይ ከተመለከትናቸው ሕጎች አንፃር ሲታይ ግን በስጦታ የመስጠትም ሆነ የማውረስ መብት በተሻለ ሁኔታ ሰፋ ብሎ የተጠበቀበት ሕግ መሆኑን እንረዳለን::

የማውረስ መብት በሕይወት ዘመን የተፈራ ሀብትን ሁሉ በመጨረሻ ማን እንደሚወስደው የሚወሰንበት በመሆኑ የገጠር መሬት ባለይዞታው በህይወት ዘመን በመሬት ላይ የሚደረግ ጥረት ሁሉ ከህይወት ዘመን ያለፈ የወደፊት የቤተሰብ ዋስትናም አድርጐ ስለሚወስደው መሬትን ለመንከባከብ ትልቅ የሚያጓጓ ምክንያት ይሆንለታል:: ከዚህም በተጨማሪ ከንብረት መብትም አንፃር በበላይ ሕግ የተደረገ ገደብ በሌለበት ሁኔታ መብቱን መገደብ ሕጋዊ ሆኖም አይታይም:: የይዞታ መብትን በስጦታ የመስጠት መብት ሽያጭ ወይም በሌላ ንብረት መለዋወጥ አይደለምና የሚከለከልበት ወይም የሚገደብበት ምክንያትም አይኖርም:: እንዲያውም የተወሰኑ የቤተሰብ አባላት መሬት ይዘው ሌሎች መሬት ባልያዙበትና በሌላ ሁኔታ መሬት የማግኘት እድል በጠበበበት ሁኔታ በቤተዘመድ መካከል መሬት በስጦታ መተላለፉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግርን ለማቃለል ከማገዙም በላይ ቤተሰባዊ ግንኙነትን ስለሚያጠናክር ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ሆኖ ይታያል::

### 3.3.2.2 የማከራየት መብት

የገጠር መሬት ባለ ይዞታ የመጠቀም መብቱን በኪራይ ማስተላለፍን በተመለከተ በክልሎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጐች መካከል በአብዛኛው ተመሳሳይነት ቢኖርም መሬት በኪራይ ሊሰጥበት የሚችለውን ከፍተኛ ዘመንና ሊከራይ የሚችለውን መሬት መጠን በተመለከተ ግን ሰፊ ልዩነት አለ:: በመሬት የመጠቀም መብትን የማከራየት መብት በሕግ መጠበቅ የሚገባው የተከራዮችን መብት ለመጠበቅ ተብሎ ሳይሆን የመሬት ባለይዞታዎች ያላቸው የመጠቀም መብት አካል ስለሆነ ነው:: የመሬት መከራየት መሠረቱ የአከራይና የተከራይ ስምምነት ቢሆንም የኪራይ ስምምነቱን ከፍተኛ የኪራይ ዘመን በሕግ መወሰኑ

---

39 በቁጥር 37 የተጠቀሰው አንቀጽ 16 (1) (3)

40 በቁጥር 37 የተጠቀሰው አንቀጽ 16 (5) እና ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11(7)

ከኪራይ ዘለዓለማዊ አለመሆንና ከውልም በጊዜ የተወሰነ መሆን ምክንያት የሚመነጭ ከመሆኑም በላይ ከውል ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታትም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህም የመሬት የኪራይ ከፍተኛ ዘመንን በሕግ መወሰኑ የንብረት መብትን እንደሚያጠብ ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ አንድ የመሬት ባለይዞታ መሬቱን የሚያከራየው ደግሞ ለፈለገው ሰው ነው፡፡ ማከራየት ሽያጭ ወይም ልውውጥ ባለመሆኑ ደግሞ አንድ ሰው የይዞታ መብቱን እንደጠበቀ መሬቱን በሙሉ ቢያከራይ ከሕጉ ጋር የሚቃረንበት ሁኔታ ስለሌለ በኪራይ የሚሰጠው መሬት መጠን መወሰን ያለበት በአከራዩ በራሱ እንጅ በክልል የመሬት አስተዳደር ሕግ መሆን አይኖርበትም፡፡

በመሬት የመጠቀም መብትን የማከራየት የሕግ መሠረትና ዓላማ ይህ ሆኖ ሳለ በኦሮሚያና በትግራይ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጐች መሠረት ግን ማከራየት የሚቻለው አንድ ሰው ካለው የይዞታ መሬት ከግማሽ ያልበለጠውን ብቻ ነው[41]፡፡ የዚህ የሚከራየውን የይዞታ መሬት መጠን በአከራዩ በመወሰን ፋንታ በመሬት አስተዳደር ሕጉ የመወሰን አስፈላጊነት ግን ሕገ መንግሥታዊ ምክንያት የለውም፡፡ የደቡብ ብሔር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ደግሞ መሬትን ማከራየት የሚቻለው ባለይዞታውን በማያፈናቅል ሁኔታ መሆን ይኖርበታል[42] በማለት ባለይዞታው ያለውን የማከራየት መብት በተዘዋዋሪ ሁኔታ የይዞታ መብትን በሙሉ ማከራየት እንደ ማይቻል በመደንገግ ገደብ ያስቀምጣል፡፡ የዚህ አዋጅ የማስፈጸሚያ ደንብ ከዚህም ባለፈ ሁኔታ ባለይዞታው ከማከራየት ቀንሶ የሚያስቀረው መሬት ቢያንስ የቤተሰቡን አመታዊ ፍጆታ የሚሸፍን ምርት የሚሰጥ መሆን እንደሚኖርበት በመደንገግ[43] ገደቡን የበለጠ ያጠናክረዋል፡፡

ይኸኛው ገደብ ደግሞ ምን ያህል መሬት ለቤተሰቡ ፍጆታ በቂ ምርት ሊሰጥ እንደሚችል ለመወሰን አስቸጋሪ በሆነበትና በተለይ ደግሞ አንዳንድ ባለይዞታዎች ያላቸው የመሬት መጠን ጠቅላላውም ቢሆን እንኳ ለቤተሰቡ አመታዊ ፍጆታ የሚበቃ የምርት መጠን መስጠት የማይችልበት እድል ባለበት ሁኔታ ባለይዞታዎች የሚኖራቸውን መሬት የማከራየት መብት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ይህ ገደብ እንዳለ ሆኖ የዚህ ሕግ መልካም ጐን ሌላ የሥራ አማራጭ ያለው ወይም ለተሻለ የሥራ እድል ወደ ሌላ አካባቢ የመሄድ ፍላጐት ያለው የመሬት ባለይዞታ ግን መሬቱን በሙሉ ማከራየት እንደሚችል በልዩ ሁኔታ መደንገጉ ነው[44]፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸው የክልል ሕጐች እንደተመለከትነው በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ላይ የሚከራየውን መሬት መጠን በተመለከተ ገደብ የተደረገው ባለይዞታዎች ከመሬታቸው እንዳይፈናቀሉ ለማድረግ ነው የሚባል ከሆነ አንደኛ ከመሬት መፈናቀል የሚከተለው ይዞታ ሲተላለፍ እንጅ የመጠቀም መብት ለተወሰነ ጊዜ በኪራይ ሲሰጥ አይደለም፡፡ ምክንያቱም መፈናቀል ማለት የይዞታ መብትን ማጣት ማለት እንጅ የመጠቀም መብትን ለተወሰነ ጊዜ ማቋረጥ ማለት ባለመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕግ በልዩ ሁኔታ መሬትን በሙሉ ማከራየት እንደሚቻል መደንገጉም ማከራየት ከይዞታ መፈናቀልን እንደማያስከትል መቀበሉን

---

41 በቁጥር 36 የተጠቀሰው አንቀጽ 10 እና በቁጥር 34 የተጠቀሰው አንቀጽ 6
42 በቁጥር 35 የተጠቀሰው አንቀጽ 8(1)
43 ደንብ ቁጥር 66/2000 አንቀጽ 8(1) (ለ)
44 በቁጥር 43 የተጠቀሰው አንቀጽ 8(1) (ሐ)

የሚያረጋግጥ ነው። ስለዚህም የገጠር መሬት ይዞታን በሙሉ ማከራየት እንደማይቻል በሕግ በመደንገግ በባለይዞታዎች የማከራየት መብት ላይ ገደብ ማድረጉ በቂ ምክንያት ያለው ሆኖ አይታይም።

የአማራ ብሔራዊ ክልል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ግን የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም ሰው የመጠቀም መብቱን ለማንኛውም ሰው በኪራይ ማስተላለፍ ይችላል[45] በማለት የደነገገ በመሆኑ በኪራይ ሊሰጥ በሚችለው የመሬት መጠን ላይ ገደብ አለማድረጉን እንገነዘባለን። ይህም ማለት በዚህ ሕግ መሠረት አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ ቢፈልግ በከፊል አለዚያም በሙሉ መሬቱን ሊያከራይ ይችላል ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ሕጉ ባለይዞታው መሬቱን ሊያከራይ ሲፈልግ ምን ያህል የመሬት መጠን ማከራየት እንዳለበት ራሱ እንዲወስን መብቱን ጠብቆለታል ማለት ነው።

የገጠር መሬት መብትን በተመለከተ በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት በባለ ይዞታዎች ላይ የተቀመጠው ክልከላ በመሸጥ ወይም በመለዋወጥ ማስተላለፍ ብቻ ሆኖ ሳለ በባለይዞታው በሚከራየው የመሬት መጠን ላይ የክልሎች ሕጎች ሊለያዩ የቻሉበት መሠረት ምን ሊሆን ይችላል ለሚለው ጥያቄ መልሱ ምን አልባት የፌዴራሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ አንቀጽ 8(1) አንድ አርሶ አደር እሱን በማያፈናቅል መልኩ ከይዞታ መሬቱ ላይ ማከራየት ይችላል በማለት ያስፈረው ድንጋጌ ሊሆን ይችላል የሚል ነው። እውነትም ``እሱን በማያፈናቅል መልኩ`` የሚለው ሐረግ አንድ የመሬት ባለይዞታ መሬቱን በሙሉ ማከራየት አይችልም የሚል መልእክት ያዘለ ይመስላል። ይሁን እንጅ ቀደም ብሎም ለማስረዳት እንደተሞከረው መሬትን ማከራየትና ከይዞታ መፈናቀል የሚገናኙ ነገሮች አይደሉም። ምክንያቱም አንድ ሰው መሬቱን በሚያከራይበት ጊዜ የሚከራየው የመጠቀም መብቱ ብቻ በመሆኑ የይዞታ መብቱ የሚቀረው ከሱ ጋር እንጅ ለተከራዩ የሚተላለፍ ባለመሆኑ መሬትን በሙሉ በማከራየት ከይዞታ መፈናቀል ሊከተል አይችልም።

የማከራየት መብት ደግሞ መሠረታዊ የንብረት መጠቀም መብት እንጅ አስተዳደራዊ ጉዳይ ባለመሆኑ በፌዴራሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ መሬት የማከራየት መብትን በከፊል መሬቱ ላይ ብቻ እንዲወሰን ማድረጉ ከፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ጋር የሚጋጭ ይሆናል። ስለዚህም የፍዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(3) በመሬት መብት ላይ ያስቀመጠው ገደብ በማከራየት መብት ላይ የሚኖር ገደብን የሚያካትት ባለመሆኑ አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን በከፊልም ሆነ በሙሉ የማከራየት መብቱ በሕግ እንዲገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት የለም።

ቀደም ብሎም ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ኪራይ ከፍተኛ ዘመን በሕግ መደንገጉ በመሬት መጠቀም መብት ላይ እንደ ገደብ የሚታይ ባይሆንም ለገደቡ መነሻ የሚሆኑት ምክንያቶች ግን በመብቱ ላይ ተዘዋዋሪ ተጽእኖ ስለሚኖራቸው ዘርዘር አድርጐ ማየቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የገጠር መሬት የሚከራይበት ከፍተኛ ዘመን በክልሎች ሕግ እንደሚወሰን በተደነገገው መሠረት በትግራይ፣ በኦሮሚያ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በአማራ ብሔራዊ ክልሎች እንደ ቅደም ተከተሉ 20 ዓመት፣ 15 ዓመት፣ 10

---

45 በቁጥር 37 የተጠቀሰው አንቀጽ 18(1)

ዓመት፣ 25 ዓመት ነው። ከፍተኛው የኪራይ ዘመን ሊለያይ የቻለበት ምክንያት፣ የመሬት አስተዳደሩ በክልሎች ልዩ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ የሚተገበር ስለሆነ አንድ ዓይነት እንዲሆን አይጠበቅም።

ይሁን እንጅ ይህ ከፍተኛ የመሬት ኪራይ ውል ዘመን ከአማራ ብሔራዊ ክልል በስተቀር በሌሎች ያለው ተፈፃሚነት መሬቱ ለአልሚ ባለሀብት በሚከራይበት ጊዜ ብቻ ሲሆን መሬቱ ልማዳዊ የአስተራረስ ዘዴ ለሚጠቀም አርሶ አደር በሚከራይበት ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው ከፍተኛ የውል ዘመን ግን ከላይ ከተጠቀሰው እጅግ ያነሰ ነው[46]። የአማራ ብሔራዊ ክልል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ግን 25 ዓመት ከፍተኛ የመሬት ኪራይ ውል ዘመኑ ለማንኛውም ተከራይ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ደንግጓል።

የመሬት ኪራይ ውል ከፍተኛ ዘመን በሕጉ መደንገግ የሚኖርበት የውልን ዘለአለማዊ ሊሆን አለመቻል መሠረት በማድረግና ተዋዋዮች በውላቸው የጊዜ ገደብ ባላስቀመጡበት ጊዜ የውሉን ክፍተት ለመሙላት እንጂ በተለይ የመሬት ኪራይን በተመለከተ የተከራዩን ማንነት መሠረት በማድረግ የሚሆንበት ምክንያት የለም። ተከራዩ ማንም ይሁን ማን የገጠር መሬት ኪራይ ዘመን ረጅም መሆንን ይፈልጋል። ምክንያቱም በመሬቱ ላይ ተከራዩ አስፈላጊውን ወጭ አድርጎ በማልማት በቂ ገቢ ለማግኘት ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። ይህ ምክንያት ደግሞ ተከራይ ለሆነው አልሚ ባለሀብትም ሆነ ልማዳዊ አስተራረስ ዘዴ ለሚጠቀመው ተከራይ አርሶ አደርም እኩል ተፈፃሚነት አለው። ከዚህም በተጨማሪ ለማንም ተከራይ የዘመኑ ረጅም መሆን ተከራዩ መሬቱን ወደፊትም ረዘም ላለ ጊዜ እንደሚጠቀምበት በማመን እንዲንከባከበውና በማልማት እንዲጠብቀው ለማድረግ ስለሚያስችል ለአከራዩም መሬቱ በእንክብካቤ እንዲያዝ በማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ከዚህም በተጨማሪ መሬቱን ለማን ማከራየት እንደሚፈልግ የመወሰን መብቱን ለአከራዩ መተው እንጅ የኪራይ ውል ከፍተኛ ዘመኑን በመለያየት መብቱን በተዘዋዋሪ መንገድ መገደቡም በቂ ምክንያት የለውም። ከሁሉም በላይ ግን በበርካታ የአገሪቱ ክፍሎች አሁን ባለው ሁኔታ የእርሻ መሬት ጥበት በመኖሩ ብዙ ልማዳዊ የአስተራረስ ዘዴ የሚጠቀሙ አርሶ አደሮች ከሌሎች አርሶ አደሮች መሬት ተከራይ በመሆናቸው የዚህ ዓይነት ተከራዮች ረዘም ያለ የኪራይ ዘመን የሚያገኙበትን የሕግ መሠረት ማስቀመጥ አስፈላጊ ስለሚሆን የኪራይ ውል ከፍተኛ ዘመኑን አንድ ዓይነት ማድረግ ያለው አስፈላጊነት የጐላ ይሆናል።

### 3.3.2.3 የመጠቀም መብትን በዋስትና ማስያዝ

አንድ ንብረት በእዳ ዋስትናነት የሚያዘው ባለእዳው እዳውን ባይከፍል ባለገንዘቡ የተያዘውን ነገር ለእዳው መክፈያ ለማድረግ እንዲችል ነው። አሁን ባለው ኢትዮጵያ የገጠር መሬት ሥሪት ሁኔታ ግን የግል የመሬት ባለቤትነት ባለመኖሩ ባለይዞታው የሌለውን የባለቤትነት መብት ለሌላ ሰው በመያዣነት ሊሰጥ አይችልም። ይሁን እንጂ የገጠር መሬት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ የይዞታና የመጠቀም መብት አለው። ባለይዞታው የይዞታ መብቱን በዋስትና ቢያስይዝ ደግሞ ግዴታውን ባልተወጣ ጊዜ ይዞታው ለባለገንዘቡ እንዲተላለፍ

---

[46] በትግራይ ብሔራዊ ክልል 3 ዓመት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል 3 ዓመት፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች 5 ዓመት ነው።

ስለሚያደርግና ይህ ደግሞ በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የተከለከለለውን መሬትን የመሸጥ ውጤት ስለሚያስከትል በሕግ የሚፈቀድ አይሆንም። ባለይዞታው ያለው በመሬት የመጠቀም መብት ግን በኪራይ ሊተላለፍ እንደሚችል ሁሉ በዋስትናም ሊያዝ ይችላል። ምክንያቱም የመሬት ባለይዞታው የመጠቀም መብቱን በዋስትና ያስያዘበትን ግዴታ ሳይወጣ ቢቀር ባለገንዘቡ የሚኖረው መብት ከመሬቱ ከሚያገኘው ምርት ገንዘቡን ማስመለስ እስኪችል ድረስ ባለይዞታውን ተክቶ በመሬቱ መጠቀም ነው።

ይህ ደግሞ የመሬት ይዞታ መብት መተላለፍን የሚያስከትል ባለመሆኑ ባለይዞታው በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ከተፈቀዱለት መብቶች አንዱ ሆኖ መታየት ይኖርበታል። ይህን የመከራከሪያ ነጥብ የበለጠ የሚያጠናክረው ደግሞ የፌዴራሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት በዋስትና መያዝ የሚችል መሆኑን በመቀበል በአንቀጽ 8(4) የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለሀብት የመጠቀም መብቱን እንደዋስትና ለማስያዝ ይችላል በማለት መደንገጉ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ከመጠቀም መብቱም በተጨማሪ ከአንድ ተከራይ የተሻለ የሆነው የይዞታ መብት ያለው አርሶ አደር በገጠር መሬት የመጠቀም መብቱን እንደዋስትና ሊያስይዝ የማይችልበት የሕግ ምክንያትም የለም።

ይሁን እንጂ የአማራ ብሔራዊ ክልልም ሆነ የሌሎች ክልሎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጎች አንድ የገጠር መሬት የተከራየ ባለሀብት በመሬቱ ላይ ያለውን የመጠቀም መብት በእዳ ዋስትናነት ማስያዝ እንደሚችል የደነገጉ[47] ቢሆንም አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ አርሶ አደር በመሬት የመጠቀም መብቱን ማስያዝ እንደሚችል ግን ምንም የደነገጉት ነገር የለም። አንድ ባለሀብት መሬት ሊከራይ የሚችለው ደግሞ ከመንግሥት ወይም ከባለይዞታ አርሶ አደር ነው።

በዚህ ምክንያትም የመሬቱ ባለይዞታ የሆነው አርሶ አደር የመጠቀም መብቱን በዋስትና የማስያዝ መብት ሳይኖረው ከሱ የተከራየው ባለሀብት ግን የተከራየውን መሬት የመጠቀም መብት በዋስትና ሊያስይዝ ይችላል የሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል። ይህም አከራዩ የሌለውንና ሊሰጥ የማይችለውን መብት ለተከራዩ የሚሰጥ በመሆኑ በሕግ አግባብ ሆኖ አይታይም። ይህ ደግሞ የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ለገጠር መሬት ባለይዞታው ከሰጠው መብት አንፃር የባለይዞታ አርሶ አደሮችን መብት የሚገድብ ሆኖ ይታያል። ስለዚህም የአማራ ብሔራዊ ክልል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የገጠር መሬት ባለ ይዞታዎችን መብት ከማስከበር አኳያ የሚታይበት አንድ መሠረታዊ ጉድለት አርሶ አደሮች የመጠቀም መብታቸውን በዋስትና ማስያዝ እንደሚችሉ አለመደንገጉ መሆኑን እንገነዘባለን።

---

47 በቁጥር 37 የተጠቀሰው አንቀጽ 19(1)

### 3.3.2.4 የመሬት ይዞታ መብት መከበር ዋስትና እና የፍትሕ መብት

የገጠር መሬት ይዞታ መብት ዋስትና የለሽ ሊሆን የሚችልባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ አርሶ አደሮች ያላቸው የመሬት ይዞታ መብት ራሱ በጊዜ የተገደበ አለመሆኑን በግልጽ በሕግ አለመደንገግ ነው፡፡ ይሕ በሕግ ካልተጠበቀ ደግሞ ይዞታው በማንኛውም ጊዜ እየተቆረሰ ለሌላ ሰው እንዲሰጥ ወይም ለሌላ ለተፈለገ ተግባር እንዲውል ለማድረግ ለአስተዳደሩ በር ስለሚከፍት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የተሰጠውን ከይዞታ ያለነመቀል መብት በአተገባበር ችግር ምክንያት ዋስትና የለሽ ያደርገዋል፡፡ ሁለተኛው ምክንያትም በየጊዜው የመሬት ሽግሽግ እንደ ሚካሄድ በሕግ መፍቀድ ነው፡፡ የገጠር መሬት ሽግሽግ ማድረግ የሚያስፈልገው መሬት ካላቸው ቀንሶ መሬት ለሌላቸው ሰዎች ለመስጠት በመሆኑ ከተቀባዩ አንፃር ፍትሐዊነቱ ባያከራክርም መሬት ከሚቀነስበት ባለመብት አንፃር ደግሞ የንብረት መብትን ስጋት የተሞላበትና ዋስትና የለሽ ያደርገዋል፡፡

ከዚህም ሌላ በተለይ እንደ አማራ ብሔራዊ ክልል ባለ መሬቱ እጅግ በተበጣጠሰበትና በተራቆተበት አካባቢ በየጊዜው የመሬት ሽግሽግ ማድረግ የሚታረሰውን የአንድ ሰው ይዞታ መጠን እጅግ እያሳነሰ ጥቅም እንዳይሰጥ ከማድረጉም በላይ በይዞታ ዋስትና ማጣት ምክንያት ለመሬት የሚደረገውን ጥበቃና እንክብካቤ በመቀነስ አካባቢው የበለጠ እንዲራቆት የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ የአንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሆንን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት ለባለይዞታው አለመስጠት ነው፡፡ የመሬት የግል ባለቤትነት በተፈቀደበት ሥሪት የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንደሚሰጥ ሁሉ ለገጠር መሬት ይዞታ መብትም ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካልተሰጠ አንዱ የመሬቱ ባለይዞታ ነኝ ባይ ከሌላው ባለይዞታ ነኝ ባይ የተሻለ መብት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የይዞታ መብት ዋስትናን በሕግ በቂ ጥበቃ የሌለው እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በዚህም ምክንያት የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ሕግ የገጠር መሬት ይዞታ መብት የጊዜ ገደብ እንደሌለው በመደንገግ የመሬት ሽግሽግንም በመርሕ ደረጃ በመከልከሉ[48] ከዚህ አንጻር ሊኖር የሚችለውን የይዞታ ዋስትና ማጣት ሥጋት እንደቀነሰው እናያለን፡፡ የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትን በተመለከተም በሕጉ ከመደንገጉም በተጨማሪ በክልሉ ለሚገኙ 96% ገደማ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች የምስክር ወረቀቱ በመስጠቱ[49] የመሬት ይዞታ ዋስትና የተሻለ የሕግ ጥበቃ አግኝቷል ማለት ይቻላል፡፡

የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መብት ጥበቃ በሕግ በበቂ ደረጃ ተደንግጓል ቢባል እንኳ መብቶቹ በሚጣሱበት ጊዜ አጥፊዎችን ለማረምና መብቱን መልሶ ለማስከበር እንዲቻል ለማድረግ ፍትሕ የማግኘት መብት ከሌለ የሕጉን ድንጋጌ ትርጉም አልባ ያደርገዋል፡፡ አርሶ አደሮች ያላቸውን የመሬት ይዞታ መብት በተመለከተ የፍትሕ መብታቸው መረጋገጥ

---

48 አንቀጽ 5(3)፣ 8(1)

49 ከአቶ ገበየሁ በላይ (የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ኤክስፐርት) ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡

እንዲችልም ፍ/ቤቶች በአግባቡ የተደራጁና ለአርሶ አደሮች ተደራሽ የሆኑ መሆን አለባቸው፡፡ ይሁን እንጅ በአማራ ብሔራዊ ክልል አዋጅ ቁጥር 148/1999 እስከ ወጣበት ጊዜ ድረስ[50] ማንኛውም የገጠር መሬት ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ በማህበራዊ ፍ/ቤቶች ታይቶ ቀጥሎ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በይግባኝ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኝ ተደርጐ ስለነበር አርሶ አደሮች ያላቸው በመደበኛ ፍ/ቤት ፍትህ የማግኘት መብት ውሱን ሆኖ ቆይቶ ነበር፡፡

የገጠር መሬት መብት ለአንድ አርሶ አደር ከፍተኛው የንብረት መብት ነው፡፡ ምክንያቱም መሬት ለአርሶ አደሩ ኑሮም፣ የማንነት መገለጫም፣ አገርም ነው፡፡ ስለዚህም አርሶ አደሩ ፍትህን ከመሬት መብት ነጥሎ ከሌላ መብት ጋር በማያያዝ ሊያይ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል በግብርና ሥራ በሚተዳደርበት አካባቢ የተቋቋመ ፍ/ቤትም ፍትህ መስጠቱን ማረጋገጥ የሚችለው ለአርሶ አደሩ የመሬት መብት ጉዳዮች ክፍት ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የመሬት ክርክር ወደ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ከተፈቀደ በፍ/ቤቶች ላይ የሥራ ጫና ይኖራል በሚል ምክንያት[51] ማንኛውም የገጠር መሬት ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ማህበራዊ ፍ/ቤት እንዲታይ ማድረጉ ትልቁን መብት አሳንሶ ማየትና ለአርሶ አደር አካባቢ ፍ/ቤት የሚያስፈልግበትን ምክንያትም መዘንጋት ይመስላል፡፡

ከ1999 ጀምሮ ግን በአማራ ብሔራዊ ክልል ማንኛውም ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃም መደበኛ ፍ/ቤት መቅረብ እንደሚችል በሕጉ በመደንገጉ የመሬት ባለይዞታዎችንም ሆነ ሌሎች ተጠቃሚዎችን መብት ለማስጠበቅ የሚያስችል የተሻለ የፍትሕ ተቋማዊ ሁኔታ አለ ማለት ይቻላል፡፡

## 4. ማጠቃለያ

የቅድመ 1967 የኢትዮጵያ የመሬት ሥሪት፣ የወል ይዞታ፣ የግል ይዞታና የመንግሥት ይዞታ በሚል የተከፈለና በውስጡም የተለያዩ ንዑስ የይዞታ ዓይነቶችን የሚያካትት ውስብስብነት የሚታይበት ሥሪት ነበር፡፡ በአንድ አገር ያለው የመሬት ሥሪት ዓይነት የመሬት ባለ ይ ዞታዎችን መብት በማስፋትም ሆነ በማጥበብ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ለንብረት መብት ዋናው መሠረት መሬት በሆነባቸውና አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በባህላዊ የግብርና ሥራ በሚተዳደርባቸው አገሮች የመሬት ሥሪቱ የመሬት ባለይዞታዎችን የንብረት መብትም ሆነ የእያንዳንዱን ባለይዞታ ማህበራዊ ደረጃ በመወሰን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በኢትዮጵያ በ1967 የመሬት ሥሪት ለውጥ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የመሬት ባለቤትነት የመንግሥት ሆኖአል፡፡ ስለዚህም መሬት በግል ባለቤትነት ሊያዝ እንደማይችል በሕግ በመደንገጉ የመሬት ተጠቃሚዎች መብት የይዞታ መብት ብቻ እንዲሆን አድርጐታል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥትም የአገሪቱ የንብረት

---

50 የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ

51 የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በክልሉ ማንኛውንም የገጠር መሬትን የሚመለከት ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣንነት ለመደበኛ ፍ/ቤት መሰጠት አለበት እንጅ በማህበራዊ ፍ/ቤት መታየት የለበትም በማለት ከአንዳንድ የክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ኃላፊዎች ጋር ካደረገው ውይይት የተገነዘበው፡፡

መብት መሠረት በአጠቃላይ የግል ባለቤትነት መብት ላይ የተመሠረተ መሆኑን በግልጽ ሲደነግግ በተለይ የመሬት ባለቤትነት ግን በመንግሥት እንደሚያዝ በመወሰኑ የገጠር መሬት ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በአሁኑ ጊዜ ያላቸው መብት የይዞታ መብት ብቻ ነው።

በንብረት ላይ የሚኖር የግል ባለቤትነት መብት ለባለቤቱ የሚሰጠው መብት ለሌና መሸጥ መለወጥን ጨምሮ በርካታ ከንብረቱ በሚገኙ አገልግሎቶች መጠቀምን የሚያካትት ነው። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ያለው የገጠር መሬት ሥሪት ለመሬት ባለይዞታዎች የሚሰጠው መብት ምን ዓይነት የንብረት መብቶችን የሚያካትት ነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ በዚህ ጽሑፍ ከፍተኛ ትኩረት የተደረገበት ነጥብ ነው።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሬትን በተመለከተ የደነገገው አንደኛ የመሬት ባለቤትነት የመንግሥትና የህዝብ ብቻ ነው፤ ሁለተኛ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የጋራ ንብረት ነው፤ ሦስተኛ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው የሚሉ ቁም ነገሮችን ነው።

ከዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ በንብረት መብትነት እንደማይኖረው ተለይቶ የተቀመጠውና አንድ የግል የንብረት ባለቤት ከሚኖረው መብትም የሚለየው መሬትን የመሸጥና የመለወጥ መብት አለመኖር ነው። ስለዚህም አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ አርሶ አደር መሬቱን ከመሸጥ ወይም በሌላ ንብረት ከመለዋወጥ በስተቀር ማንኛውም አንድ የግል ባለቤት የሚኖረው የንብረት መብት ሁሉ እንደሚኖረው በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የተፈቀደ እንደሆነ ለመገንዘብ ብዙ ክርክር የሚጠይቅ ሆኖ አይታይም።

አንድ የገጠር መሬት ባለ ይዞታ ከመሸጥ ወይም በሌላ ንብረት ከመለወጥ በመለስ የሚኖረው የንብረት መብት ደግሞ በመሬቱ በግል መጠቀምን፣ ማከራየትን፣ ማውረስን፣ በስጦታ መስጠትንና የመጠቀም መብቱን በእዳ ዋስትናነት ማስያዝን የሚያካትት ነው። እነዚህ መብቶች በሕገ መንግሥት ሳይሆን በዝርዝር ሕግ የሚደነገጉ በመሆናቸው የመሬት ይዞታ መብት በሚተገበርበት ጊዜ ሊጠቡ ወይም ገደብ ሳይደረግባቸው ተፈፃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መሠረት መሬትን የማስተዳደር መብት ለክልሎች የተሰጠ በመሆኑ የአማራ ብሔራዊ ክልልም የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ አውጥቶ የባለይዞታዎችን መብት በማስተዳዳር ላይ ይገኛል። በፌዴራሉ ሕገመንግሥት የገጠር መሬት መብትን በተመለከተ ባለይዞታው የተከለከለው መሸጥ ወይም በሌላ ንብረት መለዋወጥን በተመለከተ ብቻ በመሆኑ የክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ከነዚህ መብቶች በመለስ ባሉ መብቶች ላይ ገደብ ለማድረግ የሚያስችለው የሕግ መሠረት የለም።

ይሁን እንጅ መሬትን ማከራየትን፣ ማውረስንና በስጦታ መስጠትን በተመለከተ የአንዳንድ ብሔራዊ ክልሎች ሕጎች በኪራይ ሊሰጥ በሚችለው መሬት መጠን ወይም በኪራይ ውሉ ከፍተኛ ዘመን ወይም መውረስ በሚችለውና ስጦታ ሊሰጠው በሚገባው ሰው ላይ ገደብ ያደረጉ ቢሆንም የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕግ ግን ከዚህ በተለየ ሁኔታ ደንግጓል። በዚህ

ሕግ መሠረት በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን ለማንኛውም ሰው ከ25 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ማከራየት፣ የይዞታ መብትን በኑዛዜ ለማንኛውም በግብርና ሥራ የሚተዳደር ሰው ወይም በሕግ ለማውረስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የይዞታ መብትን ሕጉ ለዘረዘራቸው የተወሰኑ ባለመብቶች በስጦታ መስጠት እንደሚቻልም ደንግጓል፡፡ ስጦታ መስጠትን በተመለከተ የተቀመጠው ገደብ በቂ የሕግ ምክንያት ያለው ስለማይመስል ሕጉ ውሱንነት ቢታይበትም ስለማከራየትና ማውረስ የደነገገው ግን የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ከደነገገው የመሬት ይዞታ መብት ጋር የሚጣጣም ሆኖ ይታያል፡፡ ነገር ግን በክልሉ የወጡትን የገጠር መሬት ሕጐች በዝርዝር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ እስከአሁን ያልወጣ በመሆኑ ችግሮች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ የመመሪያው መውጣት ያለው አስፈላጊነት ከፍተኛ ነው፡፡

የገጠር መሬት ይዞታ መብት ብቻ በሕግ በተፈቀደበት ሁኔታ የመሬት ይዞታ መብትን በዕዳ ዋስትናነት አስይዞ የይዞታ መብትን በእዳ መክፈያነት ለባለገንዘቡ ማስተላለፍ ውጤቱ ሽያጭ ስለሚሆን በሕጉ የተከለከለ ቢሆንም የመጠቀም መብትን በዕዳ ዋስትናነት ማስያዝ ግን የሚከለከልበት ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም በዕዳ የተያዘው በመሬት የመጠቀም መብት ከሆነ ባለገንዘቡ መብት የሚኖረውም ዕዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ መሬቱን መጠቀምና በመጨረሻ የመጠቀም መብቱን ለባይዞታው መመለስ ስለሆነ የሽያጭ ወይም የመለዋወጥ ውጤት አይኖረውም፡፡

የሕግ ውጤቱ ይህ ቢሆንም የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕግ የመጠቀም መብትን የመሬት ባለይዞታ ከሆኑት አርሶ አደሮች ያነሰና የተከራይነት መብት ብቻ ላላቸው ተከራይ ባለሀብቶች ግን በዕዳ የማስያዝ መብት ፈቅዶ ለአርሶ አደሮች አለመፍቀዱ በቂ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አይታይም፡፡ በመሬት የመጠቀም መብት በዕዳ ዋስትናነት ማስያዝ ደግሞ የመሬት ባለ ይዞታው ሊጠበቅለት የሚገባ አንዱ የንብረት መብት ከመሆኑም ሌላ አርሶ አደሮች መሬታቸውን ለማልማት የሚረዳ ገንዘብ ከሕጋዊ የገንዘብ ተቋማት ጋር በመስማማት ለማግኘት የሚረዳ መንገድም በመሆኑ የመብቱ አለ መፈቀድ በመሬት በመጠቀም መብት ላይም ተጽዕኖ ስለሚኖረው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ሆኖ ይታያል፡፡

የገጠር መሬት መብት በቂ የሕግ ዋስትና እና የፍትሕ ጥበቃ ከሌለው ብዙ ትርጉም የለውም፡፡ ለአርሶ አደሮች በቂ ፍትሕ ተሰጥቷል ማለት የሚቻለው ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮች በፍትህ አካሉ ታይተው ውሳኔ የሚያገኙበት ሁኔታ ከተመቻቸ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ለአርሶ አደሩ ትልቁ መብት የመሬት መብት ነው፡፡ ማንኛውም ሀብቱም፣ ሕይወቱም ከመሬት ጋር የተሳሰረ በመሆኑ መሬትን የሚመለከት ጥያቄ ሁሉ በግል በመግባባት ችግሮችን መፍታትን በሚያበረታታ ሁኔታ በፍ/ቤት ውሳኔ ማግኘት እንዲችል ፍ/ቤቶች ለአርሶ አደሮች ተደራሽ መሆን መቻላቸው ለገጠር መሬት ይዞታ መብት መጠበቅ መሠረት ነው፡፡